በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ክርስቲያናዊ መመሪያ - ለደስተኛ ትዳር

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፦* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**የካቲት ፱ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.**

# ክርስቲያናዊ መመሪያ - ለደስተኛ ትዳር

- "እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፥ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፥ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል።" ***መዝ 126፡1፡፡***
- በርካታ ሰዎች ለተለያዩ በርካታ ምክንያቶች (ለገንዘብ፣ ልጆቻቸውን ለማሳደግ የሚያስችል ዕድሜ እንዳያልፍባቸው፣ እውነተኛው የጋብቻ ትርጉም ለማይሰጠው መቀራረብ…) ሲሉ ይጋባሉ፡፡
- በርካታ ባለ ትዳሮችም እግዚአብሔር ለነርሱ ያለው እቅድ ምን እንደሆነ ሳይረዱና ትዳሩንም ለከፍተኛ አደጋ ሊያጋልጠው በሚችል ያልጸና መሠረት ላይ በመሆን የሕይወትን ጉዞ ይጀምራሉ፡፡
- ማንኛውንም ነገር ለመገንባት (ድልድይ፣ መኪና፣ ቤት፣ ማንኛውንም ነገር…) መዋቅርና መመሪያ ያስፈልገዋል፡፡ካልሆነ ግን ፈጽሞ ለመሥራት የማያስችለው ወይም ፈጽሞ ለመሰበር የሚያበቃው አካል ጎድሎታል ማለት ነው፡፡
- ቅዱሳት መጻሕፍት ዘወትር ልናነባቸው የሚገቡ ከሁሉ የላቀ የጋብቻ መመሪያ የሚገኝባቸው ምንጮች ናቸው፡፡ ለዘላለም ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ጋር ልጆቹ ሆነን ለዘላለም እንድንኖር፣ ከሰው ሁሉ ጋር በፍቅርና በስምምነት እንድንመላለስ የምንመራበትን መርሕ ያኖረበት መዝገብ ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው፡፡
- "ብዙ ምርኮ እንዳገኘ በቃልህ ደስ አለኝ።" ***መዝ 118፡162፡፡***

## ***ቅዱስ መጽሐፍ ምንድር ነው?***

1. ለ1600 ዘመናት ያህል የተጻፈ ነው፡፡
2. ከ40 በላይ የሚሆኑ ትውልዶችን ያካተተ ነው።
3. ከ40 በላይ በሚሆኑ ጸሐፊዎች (ነገሥታት፣ የግብርና ሰዎች፣ ዓሳ አጥማጆች፣ የምርምር ሰዎች፣ …) የተጻፈ ነው።
4. በተለያየየ መንገዶች ተጽፈው የቀረቡ መድበሎችን (ታሪኮችን፣ ክርክሮችን፣ ምሳሌዎችን፣ ቅኔዎችን፣ ትንቢታትን፣…) የያዘ ነው።

## ***ቅዱስ መጽሐፍን የጻፈው ማነው?***

- የመጻሕፍቱ ጸሐፊ እግዚአብሔር ሲሆን እግዚአብሔርም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲገኝ የፈቀደውን ቃሉን በመረጣቸው የሰው ወገኖች እንዲጻፍ አድርጓል፡፡ ***ካል ጴጥ 1፡20-21፡፡***

# ክርስቲያናዊ መመሪያ - ለደስተኛ ትዳር

## ለምን?

- እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ሊገልጥ ስለወደደ፡፡
- እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወደን ሊገልጥልን ስለፈቀደ፡፡
- ከእርሱ ጋር ተዋሕደን የምንኖርበትን መንገድ ሊያመለክተን ስለፈቀደ፡፡
- እንዴት ሕይወታችንን መምራት እንዳለብን የምንኖረውም በምን መልክ እንደሆነ ሊነግረን ስለፈቀደ፡፡
- በሕይወት መንገድ ሊመራን ስለወደደ፡-
    - ፈቃዱን እንድናውቅ
    - እውነትንና ሐሰትን ለይተን እንድናውቅ
    - ግራ በተጋባ ማኅበረብ ውስጥ ሊመራን ስለወደደ
- ቅዱስ መጽሐፍን በማንበብ
    - የሰዎችን አሸናፊነት (ድል) እና ውድቀት እናውቃለን፡፡
    - የራሳችንን ጥንካሬና ድክመት እንረዳለን፡፡
    - እግዚአብሔር በመንገዳችን ሁሉ ከእኛ ጋር እንደሆነ እንማራለን፡፡
    - ራሳችንን የምናሻሽልበትንና የተሻልን ሰዎች ሊያደርጉን የሚችሉ መንገዶችን እንማራለን፡፡

## እግዚአብሔር ለእኛ ያለው እቅዱ ምንድር ነው?

- እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን እቅድ ለማወቅ የክርስቲያኖች የሕይወታቸው (ትዳርን ጨምሮ) ዋና መመሪያ የሆነውን ቅዱስ መጽሐፍን ማንበብ ያስፈልጋል፡፡ “እግዚአብሔር አምላክም አለ፡- ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።” ***ዘፍጥ 2፡8፡፡***
- እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥረው ከአካሉ የተገኘች የምትወደው፣ የምትረዳው አጋር ሴት እንድትኖረው ፈቃዱ ነበር፡፡ ከአዳም ጎን አንድ አጥንት ወስዶም ከእርሱ ጋር አንድ የምትሆን ሴትን ፈጠራት፡፡ ፡፡ “ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።” **እንዳለ** ***ዘፍጥ 2፡24፡፡***
- በመጀመሪያ የነበረው ጋብቻ ወንድና ሴት በዕድሜአቸው ሁሉ አንድ ሆነው በትዳራቸውም በእግዚአብሔር አንድ ሆነው ለእግዚአብሔር እቅድ ራሳቸውን የሚሰጡበት ወይም የሚያስረክቡበት ነበር፡፡ ፡፡ “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” **እንዳለ** ***ዮሐ 3፡16፡፡***
- እግዚአብሔር ባልና ሚስት አንድ ሥጋ ሆነው በመረዳዳት እንዲኖሩ ቢፈቅድም የራሳቸውን ፈቃድና መንገድ መከተልን መረጡ፡፡ ኃጢአትም በሕይወታቸው የበዛ ሆነ ከእግዚአብሔርም ጋር የነበረው ግኙኝነታቸውም ተበጠሰ፡፡ በዚህም የተነሳ የሰው መልካምነት ወይም ሥራ ሰውን ወደ ቀደመ ክብሩ መመለስ፣ ተድላና ደስታ ወዳለበት ገነት ማስገባት የማይቻለው ሆነ፡፡
- በሕይወታችን ቅድስና ካልተገኘብን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖረን አይችልም፡፡ ስለኛ ስላለውም ፍቅሩ ያለ ዓላማና እቅድ አልተወንም፡፡ ልጁንም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ልኮ በመስቀሉ አዳነን፤ እግዚአብሔርንም በመፍራት፣ እርስ በርሳችንም በመዋደድ እንዴት መኖር እንደሚገባን በዚህም በዘላላማዊ ርስት ከራሱና ከባህርይ አባቱ ከአብ እንዲሁም ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መገናኘት እንደሚቻለን አስተማረን፡፡

# ክርስቲያናዊ መመሪያ - ለደስተኛ ትዳር

## እግዚአብሔር ለእኛ ያለው እቅዱ ምንድር ነው?

- እግዚአብሔር ዓለምን ፈጥሮ ያዘጋጀው ለእኛ ነው። ወንድና ሴትንም በልዩ ልዩ የተፈጥሮ ሥርዓት ፈጠረ።
- ወንድና ሴትን በአካል ሁኔታ የተለያየን አድርጎ ፈጠረን።
- ወንድና ሴትን በአስተሳሰብ የተለያየን አድርጎ ፈጠረን።
- በዙሪያችን ያለውን ዓለም የምንመለከትበት ሁኔታ የተለያየ አድርጎ ፈጠረን።
- እውነትንና ሐሰትን እንድንለይ አድርጎ ፈጠረን ፈጠረን።
- የፍትሐዊነት ስሜት ያለን አድርጎ ፈጠረን።
- ምሕረትን፣ ይቅርታን፣ ትዕግሥትን የምናደርግበት ሕይወት አድሎ ፈጠረን።
- ፍቅርን፣ ደግነጽንና ርኅራኄን የምናደርግ፣ የሕይወት ረዳትም እንዲኖረን አድርጎ ፈጠረን።
- በስሜትና በፍትወትም ባልና ሚስት አንድና ፍጹም ትክክለኛና ብቸኛ ጥንዶች እንዲሆኑ አድርጎ ፈጠረ።
- ሰውነታችንን ለንክኪ፣ ለመቅመስ፣ ለድምጽ፣ ለማሽተት ምላሽ የሚሰጥ አድርጎ ፈጠረን።
- ልጆችን በመውለድ መብዛት እንድንችል ምድርንም እንድንሞላ አድርጎ ፈጠረን።

## ይህም እግዚአብሔር ለትዳራችን ያለው እቅድ ዓላማው

- እግዚአብሔር ለእና ያለውን ፍቅር ማስረዳት
- የተሻልን ሰዎች መሆን የሚቻለን በምን እንደሆነ ማስተማር
- እርስ በርስ መዋደድ
- ምድርን የቅድስና ሕይወት ባላቸው ሰዎች መሙላት
- የቅድስና ሕይወት ያላቸው ልጆችን ወይም ትውልድን ማፍራት
- ስለ ዘላለማዊ ሕይወታችን እርስ በርስ እንድንተጋገዝ ማድረግ ነው፡፡

## *በትዳር ሕይወት እርስ በርሳችን መረዳዳት የምንችለው እንዴት ነው?*

- እግዚአብሔር ጋብቻን በሥጋ የተገለጠውን አምላካችንን በሕይወታችን እንድንለብሰውና እንድንመስለው የዕድሜ ልክ የሕይወት ሂደት አድርጎ አዘጋጅቶታል፡፡ “መፋታትን እጠላለሁ፥ ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፥ ልብሱንም በግፍ ሥራ የሚከድነውን ሰው እጠላለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ እንዳታታልሉ መንፈሳችሁን ጠብቁ።” *ሚል 2:16፡፡* ለምሳሌ እግዚአብሔር የሚከተሉትን ነገሮች ያስተምረናል፡፡
    - ፍጹም ፍቅርን የማይወደዱ ሰዎችን በመንገዳችን ላይ በማድረግ
    - ሐዘንን በመቅመስ ደስታን
    - አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ በማሳለፍ በእግዚአብሔር መታመንን
    - ጫናና መጨነቅ በበዛባቸው ሁኔታዎች ውስጥ በማሳለፍ ትዕግሥትን
- እኛ እነዚህን ሁሉ ነገሮች በሕይወታችን ውስጥ ባለ በእግዚአብሔር ኃይል አማካይነት ብቻ በማከናወን ላቅ ያለ አስተሳሰብና አመለካከት ልናዳብር እንችላለን፡፡

## *ባልና ሚስት ደስተኛ የሆነ ትዳር እንዲኖራቸው ምን ዓይነት ጤናማ ትዳር እንዲኖራቸው ያስፈልጋቸዋል?*

- በሕይወታቸው እግዚአብሔርን በማስቀደም ግባቸውንም እርሱን በማገልገል ራሳቸውን ማቅረብ፣ ቃሉን ማጥናት፣ ወደርሱ መጸለይና እርሱን ማምለክ፡፡
- በትዳር በባልና ሚስት መካከል ያለውን ፍጹምነት የሚመስል እንደሌለና ግጭት መኖሩ ትክክለኛ ያልሆነ ሰው ማግባታችንን የሚጠቁም ሳይሆን ሁለቱም የየራሳቸው ብርታትና ድካም ያላቸው ሥጋ ለባሽ ሆነው እርስ በርሳቸው ፍጹማን ለመሆን የሚረዳዱበት እንደሆነ መረዳት፡፡፡
- እግዚአብሔር ባልን በቤቱ የእግዚአብሔር ወኪል አድርጎ በማስተማር፣ በመምራት፣ ሚስትንም ሆነ ልጆችን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲማሩና እንዲጠብቁት በማነቃቃት መንፈሳዊ መሪ እንዲሆን ኃላፊነት ሰጥቶታል፡፡
- ጋብቻ የዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን መሆኑን በማወቅ በደስታም ሆነ በሐዘን ፈጽሞ መዋደድ፡፡
- ፍጹም ፍቅር ምንም ዓይነት ብድራትን ሳይጠብቁ መስጠት እንደሆነ ማስታወስ፡፡

# <u>ክርስቲያናዊ መመሪያ - ለደስተኛ ትዳር</u>

## <u>*ባልና ሚስት ደስተኛ የሆነ ትዳር እንዲኖራቸው ምን ዓይነት ጤናማ ትዳር እንዲኖራቸው ያስፈልጋቸዋል?*</u>

- ራስን በመግዛት መልካም ምሳሌ መሆን፡-
  - የሥጋን ፍትወት በመቆጣጠር፣ ረሐባቸውን በመቻል፣ ስሜታቸውን በማሸነፍ፣ መጥፎ አመልን በማስወገድ፣ ሐሳባቸውን በመቆጣጠር
- ክርክር ሲኖር የማንኛውም ወገን ስህተት ቢሆን ይቅር በመባባል ጤናማ ቤትና ልጆችን መገንባት መቻል
- የደግነትን ሕግ በመለማመድ ለልጆቻቸው መልካም ምሳሌ መሆን፡፡
- አንዱ የሌላውን ፍላጎት በመረዳት ራስን ለሌላው አሳልፎ መስጠት፡፡
- መከሰስ ዘወትር ፍቅርንና የራስን በጎነት አንዲደደተርፍልን ማድረግ፡፡
- በትንሹም ሆነ በታላቁ ነገር አድናቆትን መግለጽና አብሮ በመሆን መደሰት፡፡
- ጤናማ ወዳጅነት ደስታን ለማግኘትና ችግርንም ለማሸነፍ መሠረት እንደሆነ መረዳት፡፡
- ጤናማ የሆነ ግኑኝነት ከሌለ ጤናማ ወዳጅነት ሊኖር እንደማይችል መረዳት፡፡
- በሕመም፣ በችግርና በሐዘን ጊዜ አንዱ ሌላውን ማጽናናት/ማረጋጋት፡፡
- እርስ በርስ በግልጽና በፍቅር ምንም ድብቅ ነገር ሳይኖር መነጋገር፡፡
- ችግሮችን ሁሉ በጋራ መፍታት የበለጠ እንደሚመመቀራርብ መረዳት፡፡
- በሥጋ ከሆነው መልካምነታችን በላይ በመለካታዊ ስጦታ ወደ ምናገኘው መልካምነት (መተማመን፣ እምነት፣ መከባበር፣...) ማደግን መማር፡፡
- «ይቅርታ»፣ «ተሳስቻለሁ»፣ «ይቅርታ ይደረግልኝ»፣ ... ለማለት መዘጋጀት፡፡
- ልጆቻችንን ሥርዓት ማስሰስዝ፣ ታማኞች እንዲሆኑ ማገዝ በዚህም ልባቸውን በመግዛት ወደ እግዚአብሔርና ወደ ቀጥተኛው መንገድ ለመምራት መቻል፡፡
- “አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ፥ ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው።” **<u>መዝ 39፡8፡፡</u>**
- መንፈስቅዱስ በቃሉ አማካኝነት ሕይወታችንን የሚመራና አምላካችንን ኢየሱስ ክርስቶስንም እንድንመስል የሚቀርጸው ነው፡፡
- በመቀጠልም እግዚአብሔር በዚህ ሕይወት የትዳር አጋራችንን፣ ልጆቻችንንና ሌሎችንም በኃይሉ፣ በስጦታው... እንድናገለግል ይጠቀምብናል፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org